**Hallo**
**Basel-Stadt**

Kanton Basel-Stadt

# ማህበረሰባዊ ደህንነት

የማህበራዊ ዋስትና ኢንሹራንስ ስርዓቶች
የአረጋውያን እንክብካቤ
አካል ጉዳተኝነት
ስራ አጥነት
ህመም እና አደጋ
ወላጅነት እና ቤተሰብ
ማህበራዊ እርዳታ

# የማህበራዊ ዋስትና ኢንሹራንስ ስርዓቶች

የስዊዘርላንድ ነዋሪዎች በማህበራዊ ኢንሹራንስ ከተለያዩ የአደጋ ስጋቶች ይጠበቃሉ። የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ ለምሳሌ አንድ ሰው ሥራውን ካጣ ወይም ከታመመ ድጋፍ ይሰጣሉ።. በተጨማሪም ቤተሰቦችን እና አረጋውያንን ይደግፋሉ።.

## መሰረታዊ መርሆዎች

የማህበራዊ ዋስትና የሚሸፈነው በስዊዘርላንድ ነዋሪዎች ነው። የአብሮነት መርህ ተግባራዊ ይሆናል፡ አብዛኛው ህዝብ መዋጮ የሚከፍል ሲሆን ግለሰቦች እና የተወሰኑ የህብረተሰቡ አባላቶች ደግሞ ድጋፍ/ድጎማ/ ያገኛሉ። ማህበራዊ ዋስትና በአብዛኛው ግዴታ ነው። ሆኖም ግን መዋጮዎቹ በቀጥታ ከሠራተኞች ደመወዝ ይቀነሳል። ነገር ግን ቀጣሪዎች፣ በግል ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች እና ስራ የሌላቸው የገንዘብ መዋጮ ያደርጋሉ።

## አገልግሎቶች

ማህበራዊ ኢንሹራንሱ በተወሰኑ የህይወት ሁኔታዎች ውስጥ ያሉ ሰዎችን ይደግፋል። ዕለታዊ አበል፣ ጡረታ ወይም አበል ወይም በህመም ግዜ እና በአደጋ ግዜ ወጪዎችን ይሸፍናሉ። የማህበራዊ ዋስትናዎች ኢንሹራንሶች ሁሉም በመንግስት ቁጥጥር ስር ናቸው።

## ድጋፍ ለማግኘት ምን ያስፈልጋል?

- በእርጅና ጊዜ፣ በሞት እና በአካል ጉዳት ወቅት (3ቱ ምሰሶዎች ፣ AHV/IV፣ የሙያ ጡረታ፣ የግል ጡረታ)
- በህመም ወይም በአደጋ ጊዜ (የጤና እና የአደጋ ዋስትና ኢንሹራንስ)
- በወሊድ ጊዜ (የወሊድ አበል)
- ሥራ አጥነት ሲያጋጥም (የሥራ አጥነት ዋስትና)
- ልጆች ካለዎት (የቤተሰብ አበል)

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/soziale-sicherheit/sozialversicherungssystem

# የአረጋውያን እንክብካቤ

ለአረጋውያን የጡረታ አቅርቦት ፈንድ፣ ጡረተኞች ለመኖር የሚያስችል በቂ ገንዘብ እንዳላቸው ያረጋግጣል። የስዊዘርላንድ የጡረታ ስርዓት ሶስት ምሰሶዎች አሉት፣ የአረጋውያን እና የመበለት የመድን ኢንሹራንስ (AHV)፣ የሙያ ጡረታ (የጡረታ ፈንድ) እና በፈቃደኝነት ለአረጋውያን የጡረታ አቅርቦት ፈንድ (3ኛ ምሰሶ)።

## የአረጋውያን እና የመበለቶች የመድን ኢንሹራንስ (1 ኛ ምሰሶ፣ 1. Säule)

የአረጋውያን እና የመበለቶች የመድን ኢንሹራንስ (AHV) የመንግስት ተቋም ነው። አብዛኛው አዋቂዎች ከዚህ ለመጠቀም መዋጮ መክፈል አለባቸው። መዋጮዎቹ በቀጥታ ከሠራተኞች ከወርሃዊ ደመወዛቸው ይቀነሳል። አሠሪው ግማሹን ይከፍላል። በግል ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች ወይም ሥራ የሌላቸው ሰዎች መዋጮውን እንዴት መክፈል እንዳለባቸው ከካሳ ቢሮ (Ausgleichskasse) መጠየቅ አለባቸው። AHV ለጡረተኞች ወርሃዊ ጡረታ ይከፍላል። የጡረታ መጠኑ እስካሁን በተከፈለው መዋጮ ብዛት ላይ የተመሰረተ ነው። ሆኖም ግን፣ AHV በተጨማሪም የሚቹን የትዳር ጓደኛ እና ልጆች በሞት ጊዜ (የመበለት እና ወላጅ አልባ ጡረታ) ይደግፋል። ሁሉም ሰው የግል የኢንሹራንስ ልዩ ቁጥሩን የያዘ የAHV ካርድ ይቀበላል።

## የስራ ጡረታ (2 ኛ ምሰሶ፣ 2. Säule) (DE)

ከጡረታ በኋላ የተለመደውን ህይወትዎን ለመቀጠል አብዛኛውን ግዜ AHV ብቻውን በቂ አይደለም። ለዚያም ነው ለሠራተኞች የሥራ ጡረታ ፈንድ (የጡረታ ፈንድ፣ Pensionskasse) ያለው፣ ከተወሰነ ዓመታዊ ደመወዝ በላይ ግዴታ ነው። ለዚህ መዋጮ በቀጥታ ከወርሃዊ ደመወዝ ይቀነሳል፣ አሠሪው ቢያንስ ግማሽ መክፈል አለበት። በግል ስራ የሚተዳደሩ ምንም አይነት መዋጮ መክፈል የለባቸውም። ነገር ግን ይህንን በፈቃደኝነት ማድረግ ይችላሉ፣ የራሳቸው የግል ውሳኔ ነው። በጡረታ ፈንድ ውስጥ የተቀመጠው ገንዘብ በእርጅና ጊዜ እንደ ጡረታ ወይም እንደ አንድ ጊዜ ክፍያ ይከፈላል። በአንዳንድ የተለዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥም ገንዘቡ ቀደም ብሎ ሊከፈል ይችላል፣-ለምሳሌ የግል ኩባንያ ለማቋቋም፣ ከስዊዘርላንድ ርቀው ሲኖሩ፣ የግል መኖሪያ ቤት ለመገንባት ወይም አፓርታማ ለመግዛት።

## በፈቃደኝነት ለአረጋውያን የጡረታ አቅርቦት ፈንድ (3 ኛ ምሰሶ፣ 3. Säule) (DE)

3ኛው ምሰሶ በፈቃደኝነት ለአረጋውያን የጡረታ አቅርቦት ፈንድ ሲሆን፣ ከግብር ቅነሳን ያስገኛል። ከባንክ ወይም ከኢንሹራንስ ኩባንያዎች ጋር የስምምነቱን ውል መፈጸም ይቻላል። በእርጅና ጊዜ መጠባበቂያ እንዲኖርዎት በ3 ኛው ምሰሶ ፈንድ ገንዘብ መቆጠብ ያስችላል።

## ተጨማሪ አገልግሎቶች

ምንም እንኳን አረጋውያን AHV እና የጡረታ ፈንድ ቢኖራቸውም፣ ለመኖር የሚያስችል በቂ ገንዘብ የሌላቸው አረጋውያን፣ ተጨማሪ የገንዘብ ጥቅማ ጥቅሞች (Ergänzungsleistungen). ሊያገኙ ይችላሉ። ተጨማሪ ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት ማህበራዊ ድጎማ ቢሮ ማመልከት አለባቸው። የማግኘት መብት ያለው ማን እንደሆነ በግልፅ ተቀምጧል። ተጨማሪ ጥቅማ ጥቅሞች የሚሸፈነው በግብር ከፋዮች ነው።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/soziale-sicherheit/altersvorsorge

# አካል ጉዳተኝነት

ለረጅም ጊዜ መሥራት የማይችል ወይም በጤና ምክንያት በከፊል ብቻ ሥራ መሥራት የሚችል ማንኛውም ሰው፣ እንደ ሁኔታው ከአካል ጉዳት ኢንሹራንስ (IV) የገንዘብ ድጋፍ የማግኘት መብት አለው። IV ገንዘብን ብቻ አይደለም የሚከፍለው። ከሁሉም በላይ ለኢንሹራንስ ገቢዎቹ በተለይም ወደ ሙያዊ ህይወታቸው እንዲገቡ ወይም እንደገና ወደ ስራ ዓለም እንዲገቡ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል።

## የአካል ጉዳት ኢንሹራንስ

የአካል ጉዳት መድን ኢንሹራንስ (IV) የመንግስት ተቋም ነው። አብዛኛው አዋቂዎች ከዚህ ለመጠቀም መዋጮ መክፈል አለባቸው። ለዚህ ብዙ አዋቂዎች መዋጮ መክፈል አለባቸው። መዋጮዎቹ በቀጥታ ከሠራተኞች ከወርሃዊ ደመወዛቸው ይቀነሳል። አሠሪው ግማሹን ይከፍላል። በግል ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች ወይም ሥራ የሌላቸው ሰዎች መዋጮውን እንዴት መክፈል እንዳለባቸው ከካሳ ቢሮ (Ausgleichskasse) ጋር መጠየቅ አለባቸው።

## የአካል ጉዳት ኢንሹራንስ ድጋፍ

ቢያንስ ለአንድ ዓመት በጤና ምክንያት (በአካል ወይም በአእምሮ) ፍጹም መሥራት የማይችሉ ወይም በከፊሉ ብቻ መስራት የሚችሉ፣ ከ IV ድጋፍ የማግኘት መብት አላቸው። IV ድጋፉን ልክ እንደ ወርሃዊ የጡረታ አበል ይከፍላል። ነገር ግን ይህ የሚሆነው፣ ኢንሹራንስ የገባው ሰው በአካል ጉዳቱ ምክንያት ከስራ ህይወት ጋር ሊዋሃድ በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ ነው። IV የአካል ጉዳተኞች ተስማሚ ሥራ እንዲያገኙ ይደግፋል። ከ IV ድጋፍ ለማግኘት ለማካካሻ ጽ/ቤት (Ausgleichskasse) ማመልከት ያስፈልጋል።

## ተጨማሪ አገልግሎቶች

ከ IV ድጋፍ ቢኖራቸውም ለመኖር ግን በጣም አነስተኛ ገንዘብ ያላቸው ሰዎች፣ እንደ ሁኔታው ተጨማሪ የገንዘብ ድጎማዎችን (Ergänzungsleistungen). የማግኘት መብት ይኖራቸዋል። ይህንን ድጎማ ለማግኘት ማህበራዊ ድጎማ ቢሮ ማመልከት አለባቸው። ተጨማሪ ጥቅማ ጥቅሞችን የማግኘት መብት ያለው ማን እንደሆነ በግልፅ ተቀምጧል። ተጨማሪ ጥቅማ ጥቅሞች የሚሸፈነው በግብር ከፋዮች ነው።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/soziale-sicherheit/invaliditaet

# ስራ አጥነት

**ሁሉም ሰራተኞች ለስራ አጥነት ዋስትና ኢንሹራንስ አላቸው። ሥራ አጥ የሆኑ ሰዎች ለተወሰነ ጊዜ በህጉ መሰረት የገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ። ሥራ የሌላቸው ሰዎች በክልል የቅጥር ማእከል (RAV) መመዝገብ አለባቸው። በስራ መፈለግም ይረዳቸዋል።.**

## የሥራ አጥነት ኢንሹራንስ

የስራ አጥነት መድን ኢንሹራንስ (ALV) የመንግስት ተቋም ሲሆን ለሁሉም ሰራተኞች አባል መሆን ግዴታ ነው። ወርሃዊ መዋጮ በቀጥታ ከደመወዝ ይቆረጣል፣ አሠሪው ግማሹን ይከፍላል። በግል ስራ የሚተዳደሩ ለሥራ አጥነት ዋስትና መድን አባል መሆን አይችሉም። ሥራ አጥ የሆነ ማንኛውም ሰው ከሥራ አጥ ኢንሹራንስ ፈንድ ወርሃዊ የደመወዝ ምትክ (የሥራ አጥ ድጎማ ክፍያ፣ Arbeitslosengeld) ይቀበላል። መቼ እና ምን ያህል የሥራ አጥነት ክፍያ/ድጎማ/ ማግኘት እንደሚቻል፣ በብዙ በተለያዩ መስፈርቶች ይወሰናል። ለምሳሌ ያህል ጊዜ ስራ እንደሰራና ወይም ስራ አጥ የሆነበት ምክንያት ይወስነዋል።

## በስራ አጥነት ግዜ የሚወሰዱ እርምጃዎች

ከመጨረሻው የሥራ ቀን በፊት፣ ቢዘገይ ግን በመጀመሪያው የሥራ አጥነት ቀን፣ በሚመለከተው ክልላዊ የስራ የቅጥር ማእከል (Regionales Arbeitsvermittlungszentrum, RAV) በህጉ መመዝገብ ግዴታ ነው። እዚያም ሁሉም የሚያስፈልግ ቀጣይ ሂደቶች ገለጻ ይደረግሎታል።

## ክልላዊ የስራ የቅጥር ማዕከል

ክልላዊ የስራ የቅጥር ማዕከል (RAV) ሌላ ሥራ በፍጥነት ማግኘት እንዲቻል ያግዛል። የስራ አጥነት ጥቅማጥቅም ከተቀበሉ በRAV ያሉት የምክር ቃለመጠይቆች ግዴታ ናቸው። RAV በተጨማሪም ኮርሶችን ወይም ለቅጥር የሚያግዙ ፕሮግራሞችን ይሰጣል። ከእነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ ደግሞ አስገዳጅ ኮርሶች ናቸው።. በስዊዘርላንድ ውስጥ ሰርተው የማያውቁ እና ሥራ የሚፈልጉ ሰዎች እንኳን በ RAV መመዝገብ ይችላሉ። ግን ምንም ገንዘብ አይሰጣቸውም።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/soziale-sicherheit/arbeitslosigkeit

# ህመም እና አደጋ

በስዊዘርላንድ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ሰው የአደጋ እና የጤና መድን ሊኖረው ይገባል። እነዚህ የግል ኢንሹራንስ ኩባንያዎች በአደጋ፣ በህመም ወይም በእርግዝና ወቅት ወጪዎችን ይሸፍናሉ። ሁለቱም ኢንሹራንስዎች ስዊዝ በገቡ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት ውስጥ የኢንሹራንስ ውሉ መፈጸም አለበት።

## የጤና እንክብካቤ ኢንሹራንስ (መሰረታዊ ኢንሹራንስ)

ሁሉም የስዊዘርላንድ ነዋሪዎች የጤና መድህን (መሰረታዊ ኢንሹራንስ፣ Grundversicherung) በራሱ ተነሳሽነት ውል መፈጸም አለበት። ወደ ስዊዘርላንድ የሚሄድ ማንኛውም ሰው ይህን ለመፈጸም ሦስት ወር ጊዜ አለው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ከታመሙ፣ ወጪዎቹ እንዲሁ ወደ ኋላ ታሳቢ ተደርገው ይሸፈናሉ። መሰረታዊ ኢንሹራንሶች ብዙ የግል የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎች (Krankenkassen) አቅሮት አላቸው። የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎን ለመምረጥ ነፃ ነዎት። የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎች በስዊዘርላንድ የሚኖሩትን ሁሉ መቀበል አለባቸው።

ኢንሹራንስ የገቡ ነዋሪዎች ከገቢያቸው ወርሃዊ ክፍያ/ፕሪሚየም/ ይከፍላሉ። እነዚህ ፕሪሚየሞች እንደ ጤና ኢንሹራንስ ኩባንያ ዓይነት እና እንደ ኢንሹራንስ ሞዴላቸው ይለያያሉ። ስለዚህ ዋጋ ማወዳደር ጥቅም አለው። የጤና መድን ኢንሹራንሱን ሁል ግዜ እስከ ህዳር መጨረሻ ድረስ ለሚቀጥለው ዓመት መቀየር ይችላሉ። መሰረታዊ ኢንሹራንስ ከታመሙ ወጪዎችን ብቻ ሳይሆን ለእርግዝና እና በወሊድም ግዜ ውጪዎችን ይሸፍናል።. የሚገኙት አገልግሎቶችና ጥቅሞቹ በሕግ የተደነገጉ ናቸው።

ማሳሰቢያ፡ ለጥርስ ህክምና ወይም የመነጽር ወጪዎች አብዛኛውን ጊዜ ከራስዎ ይከፍላሉ አለበለዚያ ግን በፈቃደኝነት ተጨማሪ ኢንሹራንስ ከገቡ ኢንሹራንሱ ወጪውን ይሸፍናል።

## የአደጋ ጊዜ ኢንሹራንስ

በሳምንት ከ8 ሰአታት በላይ ለሚሰሩ ሰራተኞች፣ በስራ ወቅት እና በነፃ በእረፍት ጊዜያቸው ለሚደርሱ አደጋዎች፣ በአሰሪው ድርጅት የአደጋ የመድን ዋስትና ተገብቶላቸዋል። ከዚህ ያነሰ ሰዓት የሚሰራ ሰው በነፃ በእረፍት ጊዜው ለሚደርሱ አደጋዎች፣ የአደጋ የመድን ዋስትና ስለሌለው፣ ራሱ በግሉ የአደጋ ኢንሹራንስ መግባት አለበት። ይህም በግል ስራ የሚተዳደሩ ሰራተኞች እና ስራ ለማይሰሩ ሰዎች፣ ከጤና ኢንሹራንስ ኩባንያቸው ጋር የአደጋ ኢንሹራንስ ውል መግባት አልባቸው። በግል ስራ የሚተዳደሩ ሰራተኞች ከሌሎች የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ጋር የአደጋ ግዜ ዋስትና ውል መፈጸም ይችላሉ። ኢንሹራንስ ገቢዎቹ ወርሃዊ ክፍያ መክፈል አለባቸው። ተቀጣሪ ሰራተኞች ክፍያው በቀጥታ ከደመወዛቸው ይቆረጣል።

## የፕሪሚየም የክፍያ ቅናሽ

የጤና መድን ፕሪሚየም/ክፍያ/ መክፈል የማይችሉ ሰዎች እንደሁኔታው ለመሠረታዊ ኢንሹራንስ የፕሪሚየም የክፍያ ቅናሽ (Prämienverbilligung) ሊያገኙ ይችላሉ። ቅናሹን ለማግኘት የማመልከቻ ቅጽ ማቅረብ እና ስላለው ንብረት እና ገቢ መረጃ መስጠት አለበት። ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ፣ ከሚቀጥለው ወር ጀምሮ ያነሰ ክፍያ ይከፈላል። የማህበራዊ ድጎማ ቢሮ ስለ የፕሪሚየም የክፍያ ቅናሽ መረጃ ይሰጣል እንዲሁም የምዝገባውን ማመልከቻ ይቀበላል።

## ከመሠረታዊ ኢንሹራንስ ላይ ሌላ ተጨማሪ ኢንሹራንስ መግባት

በፈቃደኝነት ከመሠረታዊ ግዴታዊው ኢንሹራንስ ሌላ ተጨማሪ የተለያዩ ማሟያ ኢንሹራንሶች (Zusatzversicherungen) ሊገቡ ይችላሉ። እነዚህ በመሠረታዊ ኢንሹራንስ ያልተሸፈኑ አገልግሎቶች፣ ለምሳሌ እንደ የጥርስ ህክምና ያሉትን ይሸፍናሉ። ተጨማሪ ኢንሹራንሶች በሁሉም የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ይሰጣል። እያንዳንዱ የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያ ከማን ጋር ውል መፈጸም እንዳለበት እና እንድሌለበት ራሱ ይወስናል። እንዲሁም እንደ ሁኔታው ውሉ በምን ዓይነት ሁኔታ መፈጸም እንዳለበት መወሰን ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/soziale-sicherheit/krankheit-und-unfall

# ወላጅነት እና ቤተሰብ

ልጅ ያለው ማንኛውም ሰው በስዊዘርላንድ ውስጥ በልጆች እና በትምህርት አበል በገንዘብ ይደገፋል። በሥራ ላይ ያሉ ሴቶች ልጅ ሲወልዱ ቢያንስ ለ14 ሳምንታት የሚከፈል የወሊድ ፈቃድ የማግኘት መብት አላቸው።

## የእናትነት የወሊድ አበል

በሥራ ላይ ያሉ ሴቶች ልጅ ሲወልዱ ቢያንስ ለ14 ሳምንታት የሚከፈል የእናትነት የወሊድ ፈቃድ (Mutterschaftsurlaub) የማግኘት መብት አላቸው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ቢያንስ 80 በመቶ የደሞዛቸውውን 80 ፐርሰንት ይከፈላቸዋል። ሥራ የሌላቸው ሴቶች ወይም መሥራት የማይችሉ ሴቶች እነሱም መብት እንዳላቸው በካሳ ቢሮ መጠየቅ አለባቸው። ይህንን በሚመለከት ልዩ ደንቦች አሉ።. ከወሊድ በኋላ ባሉት በመጀመሪያዎቹ ስምንት ሳምንታት ውስጥ እናቶች እንዲሠሩ አይፈቀድላቸውም (የወላድ ደህንነት ጥበቃ፣ Mutterschutz).

## የአባትነት የወሊድ ፈቃድ

አባቶች ከወሊድ በኋላ ለሁለት ሳምንታት የሚከፈል የአባትነት የወሊድ ፈቃድ (Vaterschaftsurlaub) የማግኘት መብት አላቸው። ከየእናትነት የወሊድ ፈቃድ ጋር ሲነጻጸር፣ የአባትነት ፈቃድ ከወሊድ ፈቃድ ተለዋዋጭ ነው፡- ሁሉንም በአንድ ጊዜ ወይም በተለያዩ ቀናት ውስጥ ማግኘት መውሰድ ይቻላል። ነገር ግን ህጻኑ ከተወለደ በስድስት ወር ውስጥ ብቻ ነው የሚቻለው።

## የቤተሰብ አበል

ማንኛውም ልጅ ያለው ሰው ከቤተሰብ አበል (Familienzulagen) በገንዘብ ይደገፋል። ይህም እስከ 16 ዓመት ለሆኑ ህጻናት ልጆች፣ የልጅ አበል እና ለወጣቶች የሙያ ስልጠና ላይ ካሉ እስከ 25 ዓመት የስልጠና አበል ይከፈላቸዋል። ስራ ያላቸው ወላጆች (የግል ስራ የሚተዳደሩትን ጨምሮ) ወይም የማይሰሩ እና አነስተኛ ገንዘብ ያላቸው ወላጆች ይህ መብት አላቸው። ለሠራተኞች የቤተሰብ አበል በየወሩ ከደመወዙ ጋር አብሮ ይከፈላቸዋል። ስለ ቤተሰብ ድጎማ አበል ተጨማሪ መረጃ ከአሠሪው ወይም ከማህበራዊ ኢንሹራንስ ተቋም ማግኘት ይቻላል። የቤተሰብ አበል መጠን ከካንቶን ወደ ካንቶን ይለያያል።

## የቤተሰብ ኪራይ ድጎማ

አነስተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች የተወሰኑ ሁኔታዎችን ካሟሉ የቤተሰብ ኪራይ ድጎማ (Familienmietzinsbeiträge). የድጋፍ ክፍያ ማመልከት ይችላሉ። የክፍያው መጠን በቤተሰቡ ገቢ፣ ንብረት እና በኪራይ መጠን ላይ የተመሰረተ ነው።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/soziale-sicherheit/elternschaft-und-familie

# ማህበራዊ እርዳታ

ማህበራዊ እርዳታ ለመኖር በጣም ትንሽ ገንዘብ ላላቸው እና ከማህበራዊ ኢንሹራንስ አነስተኛ ወይም ምንም የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙ ሰዎችን ይደግፋል። ዓላማው ሰዎች በቅርብ ግዜ ውስጥ እንደገና እራሳቸውን መንከባከብ ለማስቻል ነው። ኢንሹራንስ ሳይሆን የመንግስት ድጋፍ ነው።

## ማህበራዊ እርዳታ

ማህበራዊ እርዳታ (Sozialhilfe) በስዊዘርላንድ ውስጥ የተቸገሩ ሰዎችን ሁሉ ይደግፋል። አነስተኛ የኑሮ ወጪዎች ይሸፍናል። ከገንዘብ እርዳታ በተጨማሪ የምክር አገልግሎት ይሰጣል። ዓላማው ሰዎች በተቻለ በፍጥነት እንደገና በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉ ነው። አንድ ሰው ኑሮውን ለመደገፍ በቂ ሌላ የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኝ ከሆነ፣ የማህበራዊ ዋስትና ክፍያ አይከፈለውም። ለምሳሌ ያህል፣ እንደ የሥራ አጥነት የድጎማ ገንዘብ፣ ጡረታ፣ ደመወዝ ወይም ከዘመዶች ድጋፍን ይጨምራል። ዕዳ ቢኖርም እንኳን አይከፍልም። እንደገና በቂ የፋይናንስ ምንጭ ገቢ ሲኖርዎት፣ ገንዘቡ መመለስ አለበት። ይህ ማህበራዊ እርዳታ የሚሸፈነው በግብር ከፋዮች ነው።

## ለማህበራዊ እርዳታ ማመልከት

ለማህበራዊ ዕርዳታ ማመልከት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በሚኖርበት ማዘጋጃ ቤት የማህበራዊ አገልግሎት (Sozialdienst) ማመልከት አለበት። እዚያም ገቢዎን እና ንብረትዎን መግለፅ አለብዎት። ከዚያም የይገባኛል ጥያቄው ይረጋገጣል። ባለሥልጣኖቹ የድጋፉን መጠን እና ዓይነት እንደየ ሰዉ ደረጃ ይወስናሉ። ከእውነት የራቁ መልሶችን የሰጠ ወይም ዕውነታውን የደበቀ ሰው በህግ ይጠየቃል። ማህበራዊ አገልግሎቱ መመሪያዎችን ሊሰጥ እና ሁኔታዎችን መለወጥ ይችላል። መስፈርቱ ካልተሟላ፣ የሚሰጠው ማህበራዊ አገልግሎት እና ጥቅማ ጥቅሞች ሊቀነሱ ይችላሉ። በምክር ክፍለ ጊዜያት ውስጥ መሳተፍ ግዴታ ነው። ከእርሶ የሚጠበቀውን ሁሉ ማሟላት አለበዎት። ካሉበት ችግር ሁኔታውን እራስዎ ለመቀነስ የሚችሉትን ሁሉ እንዲያደርጉ ይገደዳሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/soziale-sicherheit/sozialhilfe